# ያባይ ነገር
## (y'abay neger)

*ኃይሌ በላይ* *(ኦታዋ መስከረም 1997 ዓ.ም.ኢ)*

ኧረ ያባይ ነገር
ለማን አቤት እንበል
ለማንስ እንንገር
ተራራ ፈንግሎ
ዛፎችን ገንድሶ
አፈሩን፣ ማዕድኑን
መሬቱንም አርሶ
ያለ ምንም ፈቃድ
ያገር ወሰን ጥሶ
ያለ የሌለዉን
በሙሉ አግበስብሶ
ሰዉ ቤት ገብቶ ያድራል
ቀን ተሌት ገስግሶ፤

አባይ!
እዉነት ያንተ ነገር
ለወሬ አይመች
ለሰዉ አይነገር
ኧረ መልስ ስጠኝ
እስቲ ልጠይቅህ
ባይመችህ ነወይ
ኑሮ ቢቸግርህ
ያላንዳች ይሉኝታ
ምንም ቅር ሳይልህ
በወላጅ እናትህ
እንዲህ መጨከንህ!
ወይስ ተቀይመህ
ስላልሰራንብህ
እጃችን አጣምረን
ዝም ብለን ስናይህ
ጉዳትህን እረስተን
በክብር እምቢልታ
አባዬ! አባዬ!
እያልን በዕልልታ
ስንሸኝህ በእስክስታ፤

ባባይ ተናገርኩ እንጂ
ከቶ እኛስ ብንሆን
መች አርፈን ተቀመጥን
ሃገራችን ብለን
በስደትም ይሁን
ትምህርት ፍለጋ
ሃገር ጥለን ወጥተን
በክረምት በበጋ
በአራቱ ማዕዘናት
የዐለማችን
እንኖር የለም ወይ
ተበታትነን፤
እናት ሃገራችን
ደጊቱ ኢትዮጵያ
አሳድጋ አስተምራ
በጥበብ በሙያ
ደረሱልኝ
ልጆቼ እያለች
ስትጠብቅ በተስፋ
የተማረዉ ሁሉ
ሃገር ጥሎ ጠፋ፤

ድሃይቱ ሃገር
ፈላጊ ዕርዳታ
ምሁር አልባ ሆና
ሁሌ ስትንገላታ
ልጆችዋ በሙሉ
ኀበዝ የሆኑት
በዕውቀት በትምህርት
ልቀዉ የመጠቁት
በልማት በዕድገት
በሚሰሩበት
ሃገር ጥለዉ ወጥተዉ
በሚያፈሩበት
አገልጋይ ሆነዋል
ላብታም ሃገራት፤

እህቶች ወንድሞቼ
አድምጡ ነገሬን
ይህን ያባይን ጉድ
እስቲ እንየዉ አብረን
እሱ እንደሆን አይሰማ
ምንም ጆሮ የለዉ
መፍሰሱ አይቀርም
ዝም ብለን ካየነዉ
ምንም ብንዘፍንለት
ብናባብለዉም
መማፀን መፀለይ
ትርጉም አይሰጠዉም
ስለዚህ እናስብ
መዝፈኑን ቀንሰን
መፍትሔ እናቅርብ፤

በሌላዉም በኩል
በስደት ያለነዉ
በትምህርት በዕዉቀት
ልቀን የመጠቅነዉ
በቅርብም ብንሆን
ወይም ከርቀት
እናት ኢትዮጵያን
ከልብ እናስባት፣
ኣንገትዋን እደፍታ
ወደ ታች እያየች
ዐይኖችዋን ሸፍና
በንባ እየታጠበች
እናት ታለቅሳለች
ልጆቼ! እያለች
በደከመ አንደበት
እኛን ትጣራለች
በተስፋ በእምነት
ትጠብቀናለች
ምን እንመልስላት?

የመሠረትነዉን
የተመቸ ኑሮ
ጥለንም ባንሄድ
ወዳገር ቤት ጉዋሮ
ባገኘነዉ ትምህርት
በገበየነዉ ዕዉቀት
መንገድ እንፈልግ
ሃገር የምንረዳበት
ኑሮአችንን ትተን
መሄድ ባንችልም
እጃችንን እንዘርጋ
በተቻለ ዐቅማችን
ለዚሁም መመሪያ
መንገድ እንዲሆነን
ውድ ሃገራችን
እንዳትባል መካን
ሴማንቲክስ ኣሳይድስን
እናንብብ ጠንቅቀን፤

ኣባይም ሄዶባት
እኛም ጠፍተንባት
ወልዳ እንዳልወለደች
ችግር ያማቻቻት
ሆና እንዳትቀር
እናት ሃገራችን
አለንልሽ እንበላት
ካለንበት ሆነን
እስዋም ደስ እንዲላት
እኛም ባለንበት
እንዲሰማን ኩራት።